## ሳምንታዊ ዜና (ጳጉሜን 1 ቀን 2000 ዓ. ም.)

**የህወሀት ከፍተኛ መኮንኖች በማዕረግ ተንበሸበሹ፤ በየጦሩ ካምፕ ውስጥ ያሉ ወታደሮች ተመረቁ፤ በኢትዮጵያ የተከሰተው ረሀብ ወደ ችጋር ተሸጋግሮዋል ተባለ፤ የተመድ የሰብአዊ ጉዳዮች ኃላፊ የአስቸኳዋይ የእርዳታ ጥሪ አቀረቡ፤ ረሀቡ ከኢትዮጵያ ሊጠፋ ነው ሲል የወያኔው ባለስለልጣን አዲሱ ለገሰ በረሀብተኛው ላይ ተሳለቀ፤ አባ ገ/መድህን የሚሊኒየም መዝጊያ በዓል ዕለት ዳንኪራ ሲረግጡ ዋሉ፤ በየደብሩ ካባ ለባሽ ደህንነቶች ሊመደቡ ነው፤ በአዲስ አበባ አመዴ ገበያ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ የፈንጅ ፍንዳታ ደርሶ 12 ሰዎች ሞቱ ከ60 በላይ ቆሰሉ »»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»**

**ከፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ ሬዲዮ ሌላም ዜና በዝርዝር ያንብቡ ………………………**

የወያኔው ቡድን ባጋጠመው ከፍተኛ የፖለቲካ ኪሳራ ምክንያት ለመሸፈን ሲል ብቻ ስርዓቱን ከአደጋ ይታደጉልኛል ለሚላቸው የወያኔ የጦር አለቆች እየመረጠ የማዕረግ ዕድገት መስጠቱ ታወቀ:: እነዚህ ማዕረግ የተሰጣቸው ከፍተኛ መኮንኖች ከደደቢት በረሀ ጀምሮ ጥይትና ውሀ ተሸክመው አቀባባይ ሆነው ያገለገሉና ዛሬ ለዚህ ማዕረግ የደረሱ መሆናቸውን የገለፁት የመከላከያ ውስጥ አዋቂ ምንጮች በተለይ ለስርዓቱ ምሰሶ ናቸው ተብለው በመለስ የታመነባቸው መሆናቸውንም ምንጮቹ አጋልጠዋል::

ከነፈሰበት ጋር የማይነፍሱ ተብሎ በመለስ ዜናዊ ውዳሴ ከተሰጣቸው መካከል የሆኑት እነዚህ ተሹዋሚ ከፍተኛ መኮንኖች 11 ሲሆኑ ከነዚህ ውስጥ 8 ያህሉ የህወሀት አባል መሆናቸውና ሁለቱ ኦህዴድና አንዱ ደግሞ ብአዴን እንደሆኑም ምንጮቹ ጨምረው ገልፀዋል::

በሰራዊቱ ውስጥ የአንድ ብሔር የበላይነት ነግሶዋል ይህ ይቀረፍ በማለት ብዙ ጊዜ ከሰራዊቱ መሀል ጥያቄ ተነስቶ ለበርካታ የሰራዊቱ አባላት መባረር ምክንያት ቢሆንም አሁንም በማን አለብኝነት በመለስ ትዕዛዝ የህወሀት ከፍተኛ መኮንኖች በማዕረግ ዕድገቱ እንዲንበሻበሹ መደረጋቸው የሰራዊቱ አባላትን መናቅ ነው ያሉት ምንጮቹ በተለይ ይህ ማዕረግ ከተሰጠ በሁዋላ በየጦሩ ክፍል ውስጥ ቅሬታ መነሳቱንም ምንጮቹ ጠቁመዋል::

የወያኔ ቡድን ስልጣን ለግሌ ብሎ ከያዘ ጊዜ ጀምሮ ሰራዊቱም ሆነ ሌላው የወያኔ አባል በስራውና በችሎታው ተመዝኖ ሳይሆን ለመለስ ማን ያጎበድዳል? መለስን እንቅፋት ሲመታው ማን ቀድሞ ይወድቃል? በሚል ዕድገት የሚሰጥ መሆኑን ያጋለጡት ምንጮቹ ይህንን ያሙዋሉ 11 ከፍተኛ መኮንኖች ማዕረጉን ለብሰዋል ሲሉም ገልፀዋል::

በዚህም መሰረት ከሜጀር ጄኔራልነት ወደ ሌተና ጄኔራልነት ያደጉ ሶስት መኮንኖች 1ኛ- ሳዓረ መኮንን 2ኛ- ታደሰ ወረደ እና 3ኛ- ምርኮኛው ባጫ ደበሌ ናቸው ያሉት ምንጮቹ ሁለቱ የህወሀት አባሎች ሲሆኑ አንዱ ደግሞ የኦህዴድን ኮታ የያዘ መሆኑን ምንጮቹ አስረድተዋል::

ሌሎቹ ደግሞ ከኮሎኔልነት ወደ ብርጋዴር ጄኔራልነት ያደጉት ደግሞ 1ኛ- ገ/ሚካኤል በየነ-ህወሀት ፤2ኛ- ክንፈ ዳኘው-ሕወሀት ፤3ኛ አከለ አሳየ -ህወሀት፤ 4ኛ-ህንጻ ወ/ጊዮርጊስ -ህወሀት፤ 5ኛ- ተክለብርሀን ካህሳይ

-ህወሀት፣6ኛ- ማአሾ በየነ-ህወሀት፣ 7ኛ- ጌታቸው ጉዲና- ኦህዴድ እና 8ኛ- ወንደሰን ተካ -ብአዴን መሆናቸው ታውቋዋል ሲሉም ምንጮቹ አስረድተዋል።

ምንም እንኳዋን ቀድሞ ለነዚህ 11 ከፍተኛ መኮንኖች ማዕረጉን መለስ ዜናዊ በደብዳቤ ቢሰጥም በየጦር ክፍሎች ውስጥ ደግሞ አለቆቻቸው የማዕረግ እድገቱን እንዲሰጡ በታዘዙት ትዕዛዝ መሰረት ከምክትል መቶ አለቅነት ጀምሮ እስከ ሌተና ኮሎኔልነት ላሉትም እንደተሰጣቸው ምንጮቹ ገልፀዋል።

በዚህም መሰረት በምዕራብ ዕዝ ወስጥ በተለይ በጎንደር በኩል ውጊያ ላይ ሰንብተው ለመጡ የጦር መኮንኖች የማዕረግ ዕድገቱን የሰጠው የዕዙ አዛዥ ሜ/ጄ/ል ስዩም ሀጎስ ሲሆን ፣የሌሎች የጦር ክፍል አዛዦችም በበኩላቸው ማዕረጉን እንዳደሉ ለማወቅ ተችሎዋል ሲሉ ምንጮቹ ጠቁመዋል።

የወያኔ አረመኔ ቡድን የስልጣን ዕድሜዬን በታማኝ መኮንኖች አማካኝነት አራዝማለሁ ብሎ በማሰብ ለኔ ላላቸው ጄኔራሎች ማደል የጀመረው ማዕረግ በተዋረድ ወደ ታችኛውም የጦሩ አባላት ዘንድ እየተሰጠ ቢሆንም የማዕረግ ዕድገት አሰጣጡ አድሎአዊነት የሰፈነበት እና የአንድ ወገን የበላይነትን ያጎናፀፈ በመሆኑ በምዕራብና በማዕከላዊ ዕዝ ሰራዊት ውስጥ ቀድሞ የነበረው ጉምጉምታ አሁንም ማስነሳቱን ምንጮች አክለው ገልፀዋል።

በሌላ በኩል ሰሞኑንም በተለያዩ የጦር ካምፖች ውስጥ ሲሰለጥኑ የነበሩ አዲስ የጦሩ አባላት እየተመረቁ ሲሆን፣ በሆለታ የጦር መኮንኖች ማሰልጠኛ ውስጥ ሲሰለጥኑ የነበሩት እጩ መኮንኖች በሌተናሌ ጄኔራል ታደሰ ወረደ አማካኝነት በምክትል መቶ አለቃ ማዕረግ እንደተመረቁ የመከላከያ ምንጮች ገልፀው ወያኔ ዙሪያውን ተወጥሮ ባለበት በአሁኑ ወቅት ችግሬን ሊያቃልሉ ይችላሉ እያለ የስልጠና ጊዜያቸውን በአግባቡ ሳይጨረሱ እያስመረቀ መሆኑንም ምንጮቹ ገልፀዋል።

ከ15 ሚሊዮን ህዝብ በላይ በሞት አፋፍ ላይ ነው ያሉት ተብሎ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰብአዊ ጉዳዮች ኃላፊ ሳይቀሩ ድንገተኛ እና ያልታሰበ ጉብኝት አድርገው ረሀብ ብቻ ሳይሆን በሀገሪቱ ህዝቦች ላይ የተፈጠረው ቸጋር ነው ብለው መግለጫ በሰጡ ዕለት የሰፈር አውደልዳይ ጎረምሳ ባህሪ የተፀናወታቸው የወያኔ ባለስልጣናት ረሀብ ከኢትዮጵያ ሊጠፋ ነው በማለት እጅግ አሳፋሪና አሳዛኝ መግለጫ መስጠታቸው በህዝቡ ውስጥ ከፍተኛ ቁጣ የቀሰቀሰ መሆኑን ከደረሰን ዘገባ ለመረዳት ተችሎዋል።

ከአዲስ አበባ 40 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ግንደበረትና ደርባ አካባቢ ሳይቀር ዜጎች የዕለት ጉርስ ለማግኘት ተቸግረው እየሞቱ ባለበት በዚህ ወቅት እብሪተኛው የወያኔ ቁንጮ ባለስልጣን አዲሱ ለገሰ ከኢትዮጵያ ረሀብ ሊጠፋ ነው እያለ በሚሞቱትና እየሞቱ ባሉት ወገኖቻችን ላይ መሳለቁ እጅግ አሳዛኝና አሳፋሪ ከመሆኑም በላይ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰብአዊ ጉዳዮች ኃላፊ የጉዳዩን አሳሳቢነት ተረድተው በኢትዮጵያ ጉብኝት ለማድረግ በመጡበት ወቅት ጩኸተን ቀሙኝ በሚል ለማደናገር ይህንን የመሰለ አሳፋሪ መግለጫ መስጠቱ ህዝቡ መበሳጨቱ ተዘግቦዋል።

ድንገተኛ ጉብኝት ለማድረግ አዲስ አበባ የገቡት የመንግስታቱ ከፍተኛ ኃላፊ ማንንም የወያኔን ባለስልጣን ሳያማክሩ በቀጥታ ረሀቡ ተከስቶ ብዙ ዜጎችን አጥቅቶዋል ወደ ተባለበት አርባ ምንጭ እና ጅጅጋ ተጉዘው በአካባቢው ያለውን ረሀብ በአይናቸው ተመልክተው እና አረጋግጠው በሀገሪቱ የተከሰተው ችግር ከረሀብ ወደ ቸጋር እየተለወጠ ነው ብለው መግለጫ በሰጡበት ወቅት ውሸት ልማዳቸው የሆኑት የወያኔ ባለስልጣናት በጀሌው አዲሱ ለገሰ አማካኝነት ረሀቡ ጠፍቶዋል ብለው መግለጫ መስጠታቸው በእጅጉ እንዳስደነገጣቸው እና እንዳስገረማቸው የገለፁት ቅርበት ያላቸው ወገኖች በሀገር ውስጥ አንድም ባለስልጣን ረሀብተኛ ወገኖቻችንን ዞር ብሎ ሳያናግራቸው ረሀቡ ከኢትዮጵያ ሊጠፋ ነው ማለታቸው ያሳፍራል ሲሉም የእርዳታ ድርጅት ውስጥ የሚሰሩ ኢትዮጵያውያን እንዳስገረመ ታውቆዋል።

ከአፈርኩ አይመልሰኝ ያለው የወያኔ ቡድን የመንግስታቱ ባለስልጣን ሲመጡ እነሱ ለድራማ ባዘጋጁት አካባቢ ጉብኝት እንዲያደርጉ የተዘጋጁ ቢሆንም እሳቸው አስቀድመው ረሀቡ የፀናበትና ችጋሩ የተፈጠረበት የት እንደሆነ መረጃ ከባልደረቦቻቸው ስለደረሳቸው አርባ ምንጭ እና አካባቢዋ ፤ኦጋዴን፤እና ሌሎችም ቦታዎች ተጉዘው ህዝቡ ከፍተኛ ችግር ውስጥ መውደቁን አረጋግጠው

15 ሚሊዮን ህዝብ ስር በሰደደ ረሀብ ውስጥ ተዘፍቀው የወገን ያለህ እያሉ እየተማፀኑ ባለበት በዚህ ወቅት አዲሱ ለገሰ ይህንን መሰል መግለጫ መስጠቱ ብቻ ሳይሆን በውጭ ሀገር በህዝቡ ስም የሚለምኑት ድርጅቶችና ሀገሮች ለራሳቸው ሊጠቀሙበት ነው ብሎ ማወጁ የወያኔ ቡድን እያምታታ እንደቆየው ሁሉ ዛሬም በዚሁ መንገድ ሊቀጥል እየሞከረ ያለ ሀሰተኛና ዋሾ ነው ሲሉ አንድ የእርዳታ ድርጅት ሰራተኛ ሲገልፁ ተደምጠዋል።

እሩቅ ያሉትን ትተን እንኩዋን በአዲስ አበባ ዙሪያ ያሉ በረሀብ የተጠቁ ዜጎችን የእርዳታ እህል እንዳይሰጣቸው እየከለከሉ አንዴ ሞቃዲሾ ሌላ ጊዜ ደግሞ የአክሱም ሀውልት ምረቃ በዓል እያሉ የሚንሸራሸሩት እነ አዲሱ ለገሰ ረሀብ ጠፍቶዋል ብለው መግለጫ መስጠታቸውን ተከትሎ ሳይውል ሳያድር ከአዲስ አበባ 50 ኪሎሜትር ርቀት ላይ በግንደበረትና በደርባ ዜጎች በረሀብ ተጠቅተው እንደ ቅጠል እየረገፉ ሲሆን፤በተለይም በምዕራብና በምስራቅ ሐረርጌ፤በምስራቅ ወለጋ፤ በራያና ቆቦ፤ በሰሜን እና በመዕራብ ሸዋ በየቀኑ ዜጎች በመሞትና በመኖር መሀል ሆነው እየተሰቃዩ መሆናቸውን ከደረሰን ዘገባ ለማወቅ ተችሎዋል።

ለ15 አመታት በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ ኃላፊነት ሲያገለግል የቆየው የወያኔ ተላላኪ ስምኦን መቻሌ ቢ .ፒ. አር. በሚል አዲስ ጥናት ሰበብ ከስልጣኑ እንዲንሳፈፍ መደረጉን የኤጀንሲው ውስጥ አዋቂ ምንጮች ገለፁ።

እንዳያማህ ጥራው እንዳይበላ ግፋው እንዲሉ የወያኔ ቡድን በይፋ ባላወጀው ይኸው የማንሳፈፍ እርምጃ ዋና ስራውን አዲስ የተሾመው ምትኩ ካሳ የተባለው ሌላው ካድሬ እንዲሰራና ለታይታ ግን ስምኦን መቻሌ እንዲሆን መደረጉን ምንጮቹ ጨምረው አስረድተዋል።ለስምኦን ስልጣን መነጠቅ ምክንያት አድርገው

የሚያቀርቡት ምንጮቹ በሀገሪቱ በተከሰተው ረሀብና በቅርቡ በሰጠው መግለጫ የወያኔን ገመና ያጋለጠ በመሆኑ ነው ሲሉም ግምታቸውን ሰንዝረዋል::

የወያኔ ባለስልጣናት ረሀቡ ከሀገሪቱ ሊጠፋ ተቃርቦዋል እያሉ የሀሰት ጥሩንባቸውን እየነፉ ባለበት ወቅትና ርሀቡ ስር ሰድዶ ከ15 ሚሊዮን ህዝብ በላይ በመኖርና ባለመኖር መሀከል እየዋለለ ባለበት በዚህ ወቅት አንድ ቀን ስለረሀብተኛ ወገኖቻችን ፀሎት ያላደረሱት እነ አባ ገ/ መድህን በቅርቡ የሚሊኒየም በዓል መዝጊያ በሚል በድግስ ሲንባሸበሹ ማሳለፋቸው ህዝበ ክርስቲያኑን ማበሳጨቱ ታወቀ::

ከህዝብ የሚሰጠውን ሙዳየ ምፅዋት እየሰበሰቡ ለጦር መሳሪያ መግዣ እየዘረገፉ ያሉት እነ አባ ገ/መድህን ህዝቡ በኑሮ ውድነትና በርሀብ የሚላስ የሚቀመስ ባጣበት በዚህ ወቅት አንድም ቀን ፀሎት እናድርግ ሳይሉ ሚሊኒየም በዓል መክፈቻ ብለው አክብረው የነበረ ሲሆን ዛሬ ጳጉሜ 2 ቀን 2000 ዓ. ም. ደግሞ የሚሊኒየም መዝጊያ ብለው ድል ባለ ድግስ ማክበራቸው ምዕመናኑን እንዳሳዘነ ስነስርኣቱን የተከታተሉ የእምነቱ ተከታዮች በብስጭት ሲገልጹ ተደምጠዋል::

የአክሱምን ሀውልት ለማክበር አክሱም ከተማ በወታደር ታጅበው ሌላ ጊዜ ደግሞ የሚሊኒየም በዓል መዝጊያ አከብራለሁ ብለው በካባ ለባሽ ደህንነቶች ጥበቃና ጥይት በማይበሳው መኪና የሚንሸራሸሩት አባ ገ/መድህን በየጊዜው በጳጳሳትና በደብር አለቆች የሚደርስባቸውን ተቃውሞ ለማክሸፍ ሲሉ ሰሞኑን አዲስ ዕቅድ ማውጣታቸው ከቤተክህነት ቢሮ የደረሰን ጥቆማ አመለከተ::

አራት ጳጳሳት በአባ ገ/መድህን ድርጊት በመናደድ ሱባኤ የገቡ ሲሆን ሌሎችም ይህንን እርምጃ ሊወስዱ ይችላሉ የተባሉትን ጳጳሳት ቤተክህነት ውስጥ የሚገኙ ካባ ለባሽ ደህንነቶች በመስደብና ሞራላቸው እንዲጎዳ በማድረግ ተቃውሞአቸውን እንዲያቆሙ ለማድረግ የተሰማሩ መሆኑን የገለፀው የደረሰን ጥቆማ በተመሳሳይ መልኩ የየደብር አለቆችንም ለመቆጣጠርና አንገት ለማስደፋት እንዲያመቻቸው በየቤተክርስቲያኑ ተመድበው የአባ ገ/መድህንን አገዛዝ ለማጠናከር መታቀዱንም ይኸው የደረሰን ጥቆማ ያስረዳል::

በሌላ በኩል ህዝቡ በርሀብ እያለቀ ባለበት በዚህ ወቅት ወደ ጣሊያን በተወሰደ በ68 ዓመቱ ወደ ሀገሩ ተመለሰ የተባለውን ሀውልት ለመትከልና እሱንም አስመልክቶ በዓል ለማክበር እጅግ ከፍተኛ ወጪ እንደወጣ ከተለያዩ አቅጣጫዎች የደረሱን ዘገባዎች አጋለጡ::

በብሔራዊ ሚሊኒየም አሰባሳቢ ኮሚቴ በተባለው ክፍል በኩል የሀገሪቱ ሀብት እየተመዘበረና እየተበዘበዘ በተለይ ለባለስልጣናት መዝናኛ እየዋለ ከመሆኑም በላይ ለበዓሉ ወጪ ተብሎ በሚሊዮን የሚቆጠር ብር ወጪ እንደተደረገ ጥቆማዎቹ አስረድተዋል::

የአክሱምን ሀውልት ለማስመለስ የተሳተፉ ወገኖች በሚል ለግለሰቦችም ከፍተኛ ዋጋ የሚያወጣ ንብረት የተሸለሙ ሲሆን፤ በዚህች ቅፅበት ግን በርካታ ወገኖቻችን እንደ አክሱም ሀውልት የመቆም ሳይሆን ቁልቁል ወደ አፈር እየገቡ መሆኑን ልብ ልንል ይገባል ሲሉም የሀገሪቱ ህዝቦች እያነቡ ሲገልፁ ተስተውለዋል::

ረቡዕ ከሰዓት በሁዋላ 11 ሰዓት ላይ በአዲስ አበባ ከተማ አመዴ ገበያ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ የተቀበረ ፈንጂ ፈንድቶ 12 ሰዎች ሲሞቱ ከ60 በላይ ደግሞ ከባድና ቀላል የመቁሰል አደጋ እንደደረሰባቸው ታወቀ::

ለአውቶቡስ ተራ ቅርብ የሆነው አመዴ ገበያ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ  በርካታ ሰዎችን በአንድ ጊዜ የሚያስተናግደው ዲኤስ ተቪ ማሳያ አዳራሽ ውስጥ የደረሰው ይኸው የፈንጅ ፍንዳታ አደጋ እንደተለመደው በብዙ ተመልካቾች ተሞልቶ እንደነበርና አደጋው በደረሰ ጊዜም በሙሉ ሊጎዱ እንደቻሉ ከቁስለኞቹ አንዱ ገልፆዋል::

የአውሮፓ ኩዋስ ጨዋታዎችን እንደወትሮው ሁሉ ለመመልከት ቦታ ቦታአቸውን ይዘው ሲከታተሉ በነበሩት ወጣቶች ላይ ይህንን የመሰለ ዘግናኝ እልቂት የፈፀመው ማን እንደሆነ በግልፅ ባይታወቅም ጉዳተኞቹ ግን ድርጊቱን የፈፀመው ወያኔና ወያኔ ብቻ ነው ሲሉ አፅንኦት ሰጥተው ይገልፃሉ::

ከዚህ ቀደም በአዲስ አበባ ከተማ በተለያዩ ቦታዎች ፍንዳታዎች የደረሱ እንደነበር ያወሱት አንድ ኢንጅነር የአሁኑ ግን ከሌሎቹ ሁሉ የተለየና አደጋው ከባድ ነው ሲሉ አስረድተው ለዚህም ነው የአደጋው መጠን እጅግ የከፋ ሊሆን የቻለው ሲሉም አብራርተዋል::

ፍንዳታው በደረሰ ጊዜ አዳራሽ ውስጥ ባሉት እና ውጭ በነበሩት ሰዎች ላይ ከሞት እስከ ቀላል የመቁሰል አደጋ የደረሰ ሲሆን፤በተለይም አዳራሹ ሙሉ በሙሉ በመፍረሱ የተነሳ 6 ሰዎች ወዲያውኑ ሲሞቱ አንዱ በማግስቱ በዚያው ፍርስራሽ ውስጥ መገኘቱንና የተቀሩትም 5 ያህሉ በየሆስፒታሉ  ህይወታቸው ሊያልፍ እንደቻለ  በወቅቱ በፍንዳታው የተጎዳው ወጣት አስረድቶዋል::

ከተጋቡ አንድ አመት ያልሞላቸው ሁለት ወጣቶች በአካባቢው ቆመው ስለትዳራቸውና ስለኑሮአቸው እየመከሩ ባለበት ወቅት ከየት መጣ ሳይባል የፍንዳታ አደጋው በመድረሱ በሁለቱም ላይ ከፍተኛ አደጋ ደርሶ በራስ ደስታ ሆስፒታል ተኝተው በመታከም ላይ መሆናቸውን የተከታተለው ዘጋቢያችን የራስ ደስታ ፤የጳውሎስ፤ የጥቁር አንበሳ፤ የየካቲት 12 እና የዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታሎች በቁስለኞች ተጥለቅልቀው ታይተዋል::

ቀኑን ሙሉ በስራ ተወጥረው ውለው አዕምሮአቸውን በስፖርት ዘና ለማድረግ ወደ አዳራሹ የገቡት እነዚሁ ወጣቶች እግረ መንገዳቸውንም ስለነገው ስራቸው እያወጉ አገር አማን ብለው በተቀመጡበት ቦታ ድንገት ሳይታሰብ ፍንዳታው በመድረሱ የነገ ውጥናቸው መና ሆነና ሁሉም ተበትነው ቀሩ ያሉት አንዲት እናት ይህንን ድርጊት ከውጭ የመጣ ሀይል ያደርገዋል ብዬ በፍፁም አልልም ይሄው አውሬው የነመለስ ነው የሚፈፅመው::አንዴ በርሀብ ሌላ ጊዜ ደግሞ  በኑሮ ውድነት የስንግ ይዞን አላላውስ ብሎን እግር ከወርች

አስሮን ባለበት ጊዜ እንኩዋን ልጆቻችን ሰርተው እንዳያበሉን እንዲህ አይነት ዘግናኝ እልቂት ማድረሱ ያሳዝናል ሲሉ የእንባ ሲቃ እየተናነቃቸው ገልፀዋል፡፡

በህዝብ ዘንድ ከፍተኛ ጥላቻ ያለበት ወያኔ የከሰረ ፖለቲካውን ለመጠገን ሲል በህዝብ ህይወትና በህዝብ ደም መነገድ ከጀመረ የቆየ ቢሆንም የዛሬው ግን አንዳችም የፖለቲካ እንቅስቃሴ ያደርጋሉ ተብሎ በፍጹም በማይጠበቁ ወጣቶች ላይ ይህንን የመሰለ ዘግናኝ እልቂት ማድረሱ አሳዘኝና አሳፋሪ ነው ያሉት ሌላው ታዋቂ ነጋዴ በዚህ ሰበብ የሚፈልገውን እንደለመደው አፍሶ ለመውሰድ ነው ሲሉ አስረድተዋል፡፡

የአክሱም ሀውልት የተተከለበት ምረቃ በዓል፣ የሚሊኒየም በዓል መገባደጃ በዓልን ለማደናቀፍ ሆን ተብሎ ሻዕቢያና ቅጥረኛው ኦነግ አደጋውን አደረሱት በማለት የተለመደ ፐሮፓጋንዳውን በመንዛት በድርጊቱ የጎደፈውን ስሙን ሊያድስ የሚፍጨረጨረው ይኸው ሰው በላ የወያኔ ቡድን ረቡዕ ነሐሴ 28 ቀን 2000 ዓ. ም. በ11 ሰዓት ላይ የፈፀመው እርኩስ ተግባር እስከመቼም ቢሆን ሲታወስ ይኖራል ሲሉ ቁስለኞቹ በምሬት ገልፀዋል፡፡

በወያኔ በብሔራዊ መረጃና ደህንነት ቢሮ ተቀነባብሮ የተከናወነው ይሄው እርኩስ ተግባር በዜጎች ላይ አሰቃቂ አደጋ ካደረሱ በሆዋላም ምንም የማያውቁት ቁስለኞችን መልሰው ትፈለጋላችሁ እያሉ ወደተለያዩ ቦታዎች እየወሰዱዋቸው እንደነበር የአይን እማኞች ገልፀው የራሳቸውን አረመኔ ተግባር ድራማ አድማቂ ለያደርጉዋቸው ሊሆን ይችላል ሲሉም ያላቸውን ግምት ሰንዝረዋል፡፡